## ማውጫ


መግቢያ......3
ክፍልአንድ......4
አጠቃላይሁኔታ......4
1.1 ዓላማ......4
1.2 ከሥልጠናውየሚጠበቅውጤት......4
1.3 የሥልጠናውወሰን......5
የማሰልጠኛ ሰነድ ሽፋን......5
1.4 የስልጠናውተሳታፊዎች......5
ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሰሩ በድርጅቱ ሠራተኝነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል።......5
1.5 ስልጠናውየሚወስደውጊዜ......5
1.6 ትርጓሜ......5
ክፍልሁለት......6
2.1 ከመቀጠርየሚገኝገቢ አይነትናምንነት......6
2.2 ሠንጠረዥ“ሀ” ከመቀጠርበሚገኝገቢላይተፈጻሚየሚሆኑመጣኔዎች......7
2.3 በአይነትየሚገኙጥቅሞችላይግብርስለማስከፈል......8
2.4 እንደዓይነትጥቅሞችየማይቆጠሩ......8
2.5 ከመቀጠርየሚገኝገቢየታክስስሌት......9
2.5.1 ጉርሻ/ ቦነስእናየአመትፍቃድላይየሚከፈልታክስንበተመለከተ......9
2.5.2 በውሉመሰረትሰራተኛሲሰናበትየሚከፈልክፍያወይምሰቨራንስ......10
2.5.3 የትርፍሰዓትክፍያስሌት......11
ክፍልሶስት......12
3.1 በሠንጠረዥ "ሠ" ያለገደብ ናበገደብከገቢግብርነፃየተደረጉገቢዎች......12
3.2 ከመቀጠርገቢጋርየተያያዙሌሎችድንጋጌዎች......18
ክፍልአራት......18
4.1 የወጪመጋራት......18
4.2 የወጪድርሻ......18
4.3 የወጪመጋራትውልናአፈፃፀም......19
4.4 ተጠቃሚውክፍያውንበገንዘብለመክፈልያሉአማራቾች፦......21
4.5 የእፎይታጊዜ......21
4.6 ማበረታቻ......21
4.7 የትምህርትማስረጃአሰጣጥእናስለቀጣይስልጠናሥርዓት......22
4.8 የወለድአከፋፈልናመጣኔ......22
4.9 የአሠሪዎችግዴታ......23
ማጠቃለያ......25

ማጣቀሻዎች..........................................................................................25

## መግቢያ

ማንኛውም ገቢ የሚያገኝ ሰው ከሚያገኘው ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ እንዳለበት በተደነገገው መሰረት ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ

አሁንካለው፣ካለፈውወይምወደፊትከሚመጣውየቅጥርውልጋርበተያያዘየሚያገኘውደመወ ዝ/ምንዳ፣አበል፣ጉርሻ፣ኮሚሽን፣የመልካምሥራአፈፃፀምማበረታቻስጦታወይምሌላየአገልግሎትዋጋክፍያ፣ ተቀጣሪው ከስራ ሲቀነስ ወይም ከስራ ሲለቅ ወይም ስራን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብ ወይም የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት፣ በዳኝነት ውሳኔ መሠረት በጥሬ ገንዘብ (በዓይነት) የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ከታክስ ነጻ ከተደረገው ውጭ፣ እንደ ገቢ ተቆጥሮ ታክስ የሚሰላበት ይሆናል።

እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚዎች መንግስት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ በመጋራት ለከፍተኛ ትምህርት ከሚወጣው ወጪ አንጻር መንግሥትን መረዳት በመሆኑ በተፈጸመው ውል መሰረት የወጪ መጋራት በገንዘብና በአገልግሎት የሚከፈል ይሆናል ።

በዚሁ መሠረት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣ ከታክስ ነጻ የሆኑ ገቢዎችና በወጪ መጋራት ላይ ግብር ከፋዮች ግዴታቸውን አውቀው ታክስ በፈቃደኝነት መክፈል እንዲችሉ አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል። በመሆኑም የታክስ ጉዳዮች ትምህርት ዳይሬክቶሬት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ከሚገኙ የታክስ ትምህርት እና መረጃ አቅርቦት የሥራ ሂደት/ቡድን ጋር በመቀናጀት የታክስ አስተዳደሩን ይበልጥ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና ተገማችነት ያለው ለማድረግ ይህን ሞጁል አዘጋጅቷል።

**ክፍልአንድ**

**አጠቃላይሁኔታ**

## 1.1 ዓላማ

በዚህ ሞጁል የሚሠለጥኑ ሠልጣኞች በሥልጠናው መጨረሻ:-

በሥልጠና ሞጁሉላይበመወያየት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008፤ የተሻሻለዉ አዋጅ 1395/2017 በደንብ ቁ.410/2009፤መመሪያ ቁጥር 1/2011፣ በወጪ መጋራት ደንብቁጥር 154/2000 እና በወጪ መጋራትመመሪያ 2/2009 አውቀው የታክስ ግዴታቸውን እንዲወጡ ማስቻል።

የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማ፤

በሞጁሉ ሥልጠና ሂደት ሠልጣኞች:-

- ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ አይነትና ምንነት ይገልጻሉ፤
- **ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ የሚከፈልበት መጣኔ በመለየት መጣኔዎቹን ይዘረዝራሉ፤**
- **ከመቀጠር የሚገኝ የአይነት ጥቅሞችን በመለየት ይዘረዝራሉ፤**

- ከመቀጠር የሚገኙ ገቢ ከታክስ ነፃ የተደረጉ እና በገደብ ነፃ የተደረጉትን ገቢዎችን ይለያሉ፤
- የወጪ መጋራት አከፋፈል ሥርዓት ያስረዳሉ።
- ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና የወጪ መጋራት ምንነት በመረዳት መብትና ግዴታቸውን ይለያሉ፤

## 1.2 ከሥልጠናው የሚጠበቅ ውጤት

ከዚህ ሥልጠና በኋላ ሠልጣኞች፡-

- ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ አጠቃላይ ዕውቀት ይኖራቸዋል፤
- ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ የታክስ አዋጁ፣ደንብ እና መመሪያዎቹ ላይ ግንዛቤ እንዲፈጠር በማድረግ የሚመለከታቸው ሁሉ የሚጠበቅባቸውን ግዴታና ኃላፊነት ተረድተው ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውን በቀላሉ መወጣት ይችላሉ፤
- የወጪ መጋራት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ በመረዳት የሚመለከታቸው ሁሉ ግዴታቸውን እንዲወጡ ያስችላቸዋል።

## 1.3 የሥልጠናው ወሰን

**የማሰልጠኛ ሰነድ ሽፋን**

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 የሠንጠረዥ "ሀ" እና "ሠ"፤ በደንብ ቁጥር 410 (በዓይነት የሚገኙ ገቢዎች) ላይ እና መመርያ ቁጥር 1/2011፤ሌሎች ተያያዥ መመሪያዎች እንዲሁም በወጪ መጋራት አዋጅ፤ ደንብ እና መመሪያ ያካተተ ይሆናል።

## 1.4 የስልጠናው ተሳታፊዎች

***ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለግብር ከፋዩ እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሰሩ በድርጅቱ ሠራተኝነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል።***

## 1.5 ስልጠናው የሚወስደው ጊዜ

ይህን ሰነድ ለማሠልጠን ዘጠኝ ሰዓት ያስፈልገዋል።

## 1.6 ትርጓሜ

- ***ደመወዝ፡-*** ***ማለት በአንድ የስራ ደረጃ ላይ የተመደቡ ሰራተኞች ለሚሰጡት አገልግሎት በቀጣሪው የሚከፈል ክፍያ ሲሆን አበልንና ጥቅማ ጥቅሞችን አይጨምርም ።***
- ***የውሎ አበል፡- ማለት ለአንድ ተቀጣሪ የትራንስፖርት፣ ለስራው ቦታ እና ለስራው ሁኔታአስቸጋሪነት የሚከፈል፣ ከመደበኛው ሥራው ቦታ ርቆ (25 ኪ..ሜ.) ሲሄድለመኝታ ፣ለምግብና ለመጠጥ እና ተዛማጅ ወጪ የሚከፈል አበል ነው***
- ***ቀጣሪ ማለት፡- ተቀጣሪን የቀጠረ ወይም ለተቀጣሪው ደመወዝ የሚከፍል ሰው ነው።***
- ***ተቀጣሪ ማለት፡-በሌላ ሰው /በቀጣሪው/ መሪነትና ቁጥጥር ስር ሆኖ አገልግሎትለመስጠት፡-በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ግለሰብ ፣የድርጅት ዳይሬክተር፣ ወይም በድርጅቱ አመራር ውስጥ ኃላፊነት የተሰጠውን ሌላ ሰው እንዲሁም ተሿሚንና የህዝብ ተመራጭን ጨምሮ የመንግስት ስራ ኃላፊን ያጠቃልላል።***

- *"አሠሪ" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተመራቂን ቀጥሮ የሚያሰራ ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት፣የግል ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም ዓለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት ሲሆን በሙያው በግሉ ስራ የተሰማራ ሰውን ይጨምራል።*
- *"ተጠቃሚ" ማለት ማንኛውም በመንግስት ተቋም ለመማርና የሚፈለግበትን ወጪ ለመክፈል ከተቋሙ ጋር ዉለታ ገብቶ የከፍተኛ ትምህርት ወይም ስልጠና የሚከታተል ተማሪ ነው*
- *"ወጪ መጋራት" ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተጠቃሚና መንግስት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚያወጣውን ወጪ የሚጋሩበት ስርዓት ነው።*

## ክፍልሁለት

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ

### 2.1 ከመቀጠርየሚገኝገቢ አይነትናምንነት፤

*ሠራተኛውካለፈው፣አሁንካለውወይምወደፊትከሚመጣውየቅጥርውልጋርበተያያዘየሚያገኘውደመወዝ/ ምንዳ፣አበል፣ጉርሻ፣ኮሚሽን፣የመልካምሥራአፈፃፀምማበረታቻስጦታወይምሌላየአገልግሎትዋጋክፍያ፣ተቀጣሪው* ከስራ ሲቀነስ ወይም ከስራ ሲለቅ ወይም ስራን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብ ወይም የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት፣ በዳኝነት ውሳኔ መሠረት በጥሬ ገንዘብ (በዓይነት) የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ከታክስ ነጻ ከተደረገው ውጭ፣ እንደ ገቢ ተቆጥሮ ታክስ የሚሰላበት ይሆናል : :

- አንድ ተቀጣሪ ከመቀጠር የሚያገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የመነጨ ነው የሚባለው ፤-
    - ክፍያው የሚፈፀመው ስፍራ ግምት ውስጥ ሳይገባ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከናወነው የቅጥር አገልግሎት የተገኘ ገቢ ወይም
    - የቅጥር አገልግሎቱ የትም ቢከናወን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ስም ክፍያው ለተቀጣሪው ከተፈፀመ ነው።
- ተቀጣሪው ከመቀጠር በሚያገኘው ገቢ የሚገኘው ገቢ ለማግኘት የሚያወጣው ማንኛውም ወጪ በተቀናሽ ሊያዝለት አይችልም።

***<u>ሙከራ ፡-</u>*አንድ**

ሰልጣኞች ከመቀጠር የሚገኝ  ገቢ አይነትና ምንነትን ይገልጻሉ?

## 2.2 ሠንጠረዥ"ሀ"ከመቀጠርበሚገኝገቢላይተፈጻሚየሚሆኑመጣኔዎች

| ተቁ | በየወሩከመቀጠርየሚገኝገቢበብር | ከመቀጠርበሚገኝገቢላይተፈፃሚየሚሆንምጣኔ | የተቀናሽመጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | 0-2,000 | 0% | 0.00 |
| 2 | 2,001-4,000 | 15% | 300 |
| 3 | 4,001-7,000 | 20% | 500 |
| 4 | 7,001-10,000 | 25% | 850 |
| 5 | 10,001-14,000 | 30% | 1,350 |
| 6 | ከ 14,000 በላይ | 35% | 2,050 |

<u>የደመወዝ ገቢ የታክስ ስሌት</u>

<u>ምሳሌ</u> 1፡-ዶ/ር አበበ በ XYZ ካምፓኒ ተቀጥረው የሚሰሩ ሲሆን በወር 18,500 ብር ይከፍላቸዋል። ዶ/ር አበበ ለመንግስት ምን ያህል ግብር ይከፍላሉ?

<u>መልስ፡-</u>

የዶ/ር አበበ ደመወዝ በሠንጠረዥ "ሀ" መሰረት ከ 14,000 ብር በላይ ነው። ስለዚህ

ግብር = የወር ደመወዝ X የማስከፈያ መጣኔ - ተቀናሽ

ግብር = 18,500 x 35% - 2,050.00

ግብር = 4,425.00

አጠቃላይ ደመወዝ - ተቀናሽ ግብር

ሌሎች ወጪዎችን ሳይጨምር ተከፋይ ደመወዝ = 18,500-4,425 = **14,075.00**

- ማንኛውም ቀጣሪ ተቀጣሪው መክፈል የሚኖርበትን ግብር ከተቀጣሪው ገቢ ላይ ሳይቀንስ ራሱ ለተቀጣሪው በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለለት እንደሆነ፣ በቀጣሪው የተከፈለው የግብር መጠን ተቀጣሪው ከመቀጠር ከሚያገኘው ግብር በሚከፈልበት የገንዘብ መጠን ላይ ተደምሮ ግብሩ ይሰላል።

<u>ሙከራ፡</u>- ሁለት

**ሠልጣኞች ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ታክስ የሚከፈልበት መጣኔ በመለየት መጣኔዎቹን ይዘርዝሩ?**

### 2.3 በአይነት የሚገኙ ጥቅሞች ላይ ግብር ስለማስከፈል

- የገቢ ግብር ደንብ (410/2009) በዓይነት ለተቀጣሪው የሚሰጥ ጥቅማ ጥቅም ዋጋና ግብር የሚሰላበትን ሁኔታ፡-

- ከዕዳ ነጻ የመደረግ፤(ቀሪ የተደረገ የዕዳ መጠን)
- የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች፤(የቤትሰራተኛ፣ምግብአብሳይ፣ሹፌር፣አትክልተኛ)፣የመኖሪያ ቤት፤
- የቅናሽ ወለድ ብድር፤(ከገበያው የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ የሚያንስ)

- የምግብ ወይም መጠጥ አገልግሎት፤
- የግል ወጪዎች፤(ለተቀጠሪው የግል ወጪ ጥቅም የሚያስገኝ፣የተከፈለ ክፍያ...)
- የንብረት ወይም አገልግሎቶች፤
- የንብረቱን/አገልግሎቱን እንደመደበኛ የሚያቀርብ ከሆነ የዋጋውን 75% ወይም
- በሌላ ሁኔታ የንብረቱን/አገልግሎቱን መሸጫ ዋጋ፣
- የአየር ቲኬት ከሆነ ኢኮኖሚ ደረጃ የሚከፈለው ዋጋ
- የሠራተኞች የአክሲዮን ዐቅድ፤(ባለ አክስዮን የመሆን መብት/ምርጫ...)
- የተሽከርካሪ፤(ተሽከርካሪውን ለማግኘት የወጣ ወጪ ወይም ኪራይ (ሀ)*5%/12)
- ሌላ የዓይነት ጥቅም።

## 2.4 እንደዓይነት ጥቅሞች የማይቆጠሩ

- በሠንጠረዥ "ሠ" ከገቢ ግብር ነጻ የሆኑ ገቢዎች መሠረት ከግብር ነጻ የተደረገ ጥቅም፤
- ቀጣሪ ተመሳሳይ ጥቅም የሚያቀርብበትን ድግግሞሽ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዋጋው አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ማስላቱ ምክንያታዊ ያልሆነ እና ለአስተዳደር የማያመች ጥቅም፤
- በቀጣሪው ወይም በቀጣሪው ስም በሚተዳደር የሠራተኞች ምግብ ቤት፣ ካፊቴሪያ ወይም የመመገቢያ ክፍል ያለምንም ልዩነት ለመደበኛ ሠራተኞች ጥቅም ብቻ ተብሎ የሚቀርብ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ድጎማ፤
- የሥራ አመራር አካል ላልሆነ ተቀጣሪ በሩቅ ሥፍራ የሚቀርብ የማረፊያ ወይም የመኖሪያ ቤት አገልግሎት፤
- ተቀጣሪው እንዲጠቀምበት በቀጣሪው የሚቀርብ ተንቀሳቃሽ ስልክ፤
- በቀጣሪው በቀረበ የተንቀሳቃሽ ስልክ የተደረገን ጥሪ ጨምሮ ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚሸፍነው የተንቀሳቃሽ ስልክ ጥሪዎች ወጪ፤
- በዩኒቨርሲቲ፣ በኮሌጅ ወይም በጎልማሶች ትምህርት በሚሰጥ ሌላ ተቋም የሚሰጥ ትምህርት መከታተል እንዲችል ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚፈጽመው የትምህርት ወይም ሥልጠና ክፍያ፤
- ለተቀጣሪ ጥቅም የሚቀርብ የደህንነት ጥበቃ አገልግሎት፤
- ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና የምግብ አገልግሎት የሚያቀርቡ ሌሎች ተቋሞች ለተቀጣሪዎቻቸው የሚያቀርቡት የምግብና መጠጥ አገልግሎት፤
- ለተቀጣሪዎች የሚቀርብ የደንብ ልብስ እና የሥራ መገልገያ ።
- በማንኛውም ሁኔታ በዓይነት ጥቅሞች ላይ የሚከፈለው ጠቅላላ ግብር ተቀጣሪው በወሩ ከሚያገኘው የደመወዝ ገቢ አስር በመቶ (10%) መብለጥ የለበትም።

**<u>ሙከራ</u>፡-ሶስት**

**ሠልጣኞች ከመቀጠር የሚገኝ የአይነት ጥቅሞችን በመለየት ይዘርዝሩ?**

## 2.5 ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ የታክስ ስሌት

### 2.5.1 ጉርሻ/ ቦነስ እና የአመት ፍቃድ ላይ የሚከፈል ታክስን በተመለከተ

ጉርሻ/ቦነስ/፤የዓመትፈቃድ እና የመሳሰሉት ክፍያዎች የ 12 ወራት ጥቅም ስለሆኑ ተጠቃለው ከተደመሩ በኋላ ለ 12 ተካፍለው የተገኘው ውጤት መደበኛ ደመወዝ ላይ ከተደመረ በኋላ የሥራ ግብሩ እንዲሰላ እና የተገኘው የሥራ ግብር ክፍያ ቀደም ሲል በወር ደመወዙ የከፈለው ግብር ተቀንሶ የእያንዳንዱ 12 ወር የግብር ልዩነት በመደመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

የጉርሻ/ቦነስ ታክስ አከፋፈል፡-

ምሳሌ፡**-2** አቶ አየለ በ XYZ ካምፓኒ የድርጅቱሲኒየር አካውንታት ሆነው ተቀጥረዋል ፡፡ ድርጅቱ በወር 21,300 ብር ደመወዝ የሚከፍላቸው ሲሆን በ 2017 ዓ.ም ባሳዩት ውጤታማ የስራ አፈጻጸም የወር ደሞወዛቸውን በዓመቱ መጨረሻ በቦነስ መልክ ቢከፍላቸው አቶ አየለ ካገኙት ቦነስ ላይ መክፈል የሚጠበቅባቸው የስራ ግብር ስንት ነው?

መልስ

1. 21,300/12=1,775 +21,300 = 23,075.00
2. 23,075*35/100-2050=6,026.25
3. 21,300*35/100-2050=5,405
4. 6,026.25-5,405=621.25*12= **7,455.00** ብር የመጨረሻ የቦነስ ተከፋይ የስራ ግብር ይሆናል፡፡

የአመት ፍቃድ በገንዘብ ተቀይሮ ሲሰጥ ስለሚከፈል የስራ ግብር

የአመት ፍቃድን በተመለከተ አንድ ዓመት ያገለገለ የግል ድርጅት ሰራተኛ 16 ቀን የዓመት ፍቃድ የሚሰጠው ሲሆን ከአንድ ዓመት በላይ ያገለገለ ሠራተኛ በየሁለት ዓመቱ አንድ የሥራ ቀን እየታከለበት የዓመት እረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡

ምሳሌ፡**-3** አቶ አበበበ XYZ ካምፓኒ በድርጅቱተቀጥረው የሚሰሩሲሆኑ በድርጅቱ 28 ዓመት ያገለገሉ ሲሆን 16,500 ብር ደመወዝ ይከፈላቸዋል፡፡ አቶ አበበ በ 2016 ዓ.ም ያልተጠቀሙት 30 ቀናት የአመት ፍቃድ በገንዘብ ተቀይሮ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት በመጨረሻው ዓመት ሂሳቡ ተሰልቶ ተሰጣቸው፤

1. የአመት ፍቃዳቸው በገንዘብ ተቀይሮ ከተሰጣቸው ገንዘብ ላይ ምንያህል የስራ ግብር ይከፍላሉ?

መልስ፡-

1. 16,500/12=1,375
2. 1,375+16,500=17,875.00
3. 17,875.00*35/100 - 2,050 = 4,206.25
4. 16,500*35/100 - 2,050 = 3,725
5. 4,206.25-3,725=481.25
6. 481.25*12= **5,775** ብር ተከፋይ የስራ ግብር ይሆናል፡፡

**2.5.2** **በውሉ መሰረት ሰራተኛ ሲሰናበት የሚከፈል ክፍያ ወይም ሰቨራንስ**

በውሉ መሰረት ሰራተኛ ሲሰናበት የሚከፈል ክፍያ ወይም ሰቨራንስ ክፍያው የሚፈጸመው ሰራተኛው ሲሰናበት የሚያገኘውን የወር ደመወዝ መሰረት በማድረግ ይሆናል።በዚህም መሰረት ሰራተኛው ሲሰናበት የመጀመሪያ ደመወዙን ሙሉ በሙሉ የሚከፈለው ሲሆን ቀጥሎ ያሉት የአገልግሎት አመታት የደመወዙን 1/3 ኛ የሚከፈል ይሆናል።

ምሳሌ፡-4 ዶ/ር ከበደበ YZ ካምፓኒ የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ሲሆኑ በድርጅቱ በነበራቸው ቆይታ በወር 30,500 ብርይከፈላቸው ነበር ዶ/ር ከበደ በውላቸው መሰረት 8 አመት ሰርተው ድርጅቱ ከስራ አሰናበታቸው።

1. ተሰናባቹ ግለሰብ ከስራ ሲሰናበቱ ስንት ብር ሊከፈላቸው ይገባል?
2. ከሚከፈላቸው የስንብት ክፍያ ላይ ስንት ብር ለገቢ ባለስልጣኑ የስራ ግብር መክፈል ይኖርባቸዋል?

መልስ፡-

1. ሰራተኛ ሲሰናበት ለመጀመሪያ የወር ደመወዙን መቶ ፐርሰንት ይከፈለዋል
2. ቀጥሎ ላሉት አገልግሎቶችየደመወዙን 1/3 ኛ የሚከፈል ይሆናል
3. በዚህም መሰረት 30,500 ብር የወር ደመወዝ ለመጀመሪያው ዓመት መቶ ፐርሰንት የሚከፈለው ሲሆን በቀሩት ዓመታት የወር ደመወዙ በ 1/3 ኛ እና በቀሩት አመታት ይባዛል። በዚህም መሰረት
4. 30,500 ለመጀመሪያው አመት መቶ ፐርሰንት
5. 30,500*1/3*7 አመት=71,166.67
6. 30,500+71,166.67=101,666.67
7. 101,166.67/30,500= የ 3.32 ወር ደመወዝይከፈለዋል።
8. 30,500*35/100-2050 = 8,6255*3 = 25,875
9. 30,500*0.32 = 9,760
10. 9,760*25/100-850=1,590.00
11. 25,875+1,590= **27,465** የመጨረሻው የስንብት ክፍያ የስራ ግብር ይሆናል::

**2.5.3** **የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስሌት**

| ተቁ | የትርፍ ሰዓት የተሰራበት ሠዓት/ቀን/ | የክፍያ ሁኔታ |
|---|---|---|
| 1 | ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት | በመደበኛ ሰዓት ክፍያው በ 1.5 ተባዝቶ ይከፈላል |
| 2 | ከምሽቱ 4 ሰዓት እስከ ንጋቱ 12 ሰዓት | በመደበኛ ሰዓት ክፍያው በ 1.75 ተባዝቶ ይከፈላል |
| 3 | በሳምንት የዕረፍት ቀን የተሰራ የትርፍ ሰዓት | በመደበኛ ሰዓት ክፍያው በ 2 ተባዝቶ ይከፈላል |
| 4 | በበዓላት ቀናት የተሰራ የትርፍ ሰዓት | በመደበኛ ሰዓት ክፍያው በ 2.5 ተባዝቶ ይከፈላል |

በወሩ ውስጥ ሰራተኛው ያገኘውን የትርፍ ሰዓት ክፍያ በወሩ ከሚያገኘው ደሞወዝ ላይ በመደመር ጠቅላላ በተገኘው ገቢ ላይ በሰንጠረዥ "ሀ" መሰረት ግብር ይከፈልበታል።

ምሳሌ፡**-5** በወር 15,000 ብር ደሞወዝ የሚከፈለው ባለሙያ በሳምንት የዕረፍት ቀን የትርፍ ሰዓትበወር ውስጥ 20 ሰዓት ቢሰራ

1. የትርፍ ሰዓት ክፍያው ስንት ነው?
2. የሚከፈል የስራ ግብር ስንት ይሆናል

<u>የስሌቱ ቀመር</u>

| |
|---|
| የቀን ደመወዝ = የወር ደመወዝ/ለ 30 ቀን<br>በሰአት የሚከፈለው ክፍያ= የቀን ደመወዝ/ በቀን ውስጥ ለሚሰራው ሰዓት |

በሰዓት የሚከፈለው ክፍያ = 500/8 = 62.5

**<u>የታክሱ ስሌት፡-</u>**

በትርፍ የሰራው የሰዓት ብዛት X በሰዓት የሚያገኘው ክፍያ X መጣኔ=

20 X 62.5 X 2 = 2,500

15,000 + 2,500 = 17,500

17,500 x 35% -2,050 = **4,075.00** ግብር ይከፋላል

**ክፍልሶስት**

## 3.1 በሠንጠረዥ "ሠ" ያለገደብ እና በገደብ ከገቢ ግብር ነፃየ ተደረጉ ገቢዎች

### 3.1.1 ያለ ገደብከ ገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች

- ሠራተኛው ሲታመም አሠሪው ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ፤
- የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወይም የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የቦርድ አባል ወይም ፀሐፊ እንዲሁም የፌደራልና የክልል መንግሥታት ወይም የከተማ አስተዳደሮች በሚያቋቁሚቸው የጥናት ቡድኖች አባል ወይም ፀሐፊ በመሆን የሚከፈል አበል፤
- ለሠራተኛው ጥቅም ተብሎ ከተቀጣሪው የወር ደመውዝ 15% (አሥራ አምስት በመቶ) ባልበለጠ መጠን በየወሩ በቀጣሪው የሚዋጣ የጡረታ መዋጮ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ፤
- በመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ  እና በግል ድርጅት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ከግብር ነፃ የተደረገ የጡረታ ገቢ፤
- የኢትዮጵያ የፌደራል፣ የክልል ወይም የአካባቢ መንግሥታት ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከመደበኛ ሥራዎቻቸው ጋር በተያያዘ የሚያገኙት ገቢ፤
- በዓለም ዐቀፍ ስምምነት መሠረት ከግብር ነፃ የሆነ የገቢ መጠን፤
- በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በተደረገ ስምምነት መሠረት ማናቸውም ገቢ ከግብር ነፃ የሚሆነው፡- ስምምነቱየተደረገውለመንግሥት የገንዘብ፣የቴክኒክ፣ሰብአዊ ወይም አስተዳደራዊ እርዳታ ለማቅረብ የሆነ እንደሆነ እና ከግብርነፃማድረግየሚያስችለውንአንቀጽበሚመለከትሚኒስትሩመስማማቱንበጽሁፍሲገልጽ

- በማንኛውም መስክ ለላቀ የሥራ ክንውን የሚሰጥ ሽልማት፤
    - አንድን ቴክኖሎጅ ለማሻሻል፣አዲስ የፈጠራ ስራ በመስራት ወይም ወጪን ለመቀነስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ስራ ላይ በማዋል የሚሰጥ ሽልማት
    - በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረግ ውድድር አገርን ወክሎ ወይም በሀገር አቀፍ ደረጃ በህግ በተቋቋመ ድርጅት በሚደረግ ማንኛውም ውድድር የሚሰጥ ሽልማት
    - በፌደራል፣ በክልል፣ በአዲስ አበባ እና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር መንግስት የላቀ የስራ ክንውን ላስመዘገበ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚሰጥ ሽልማት ሲሆን ሽልማቱ ከገቢ ግብር ነጻ ሊሆን የሚችለው ከፈጠራ ስራው ጋር ግንኙነት ያለው የመንግስት አካል ለፈጠራ ስራው እውቅና የተሰጠው ወይም የፈጠራ መብት ሲኖረው ነው ።
- በተቀባዩ ላይ በደረሰ ጉዳት ወይም በሌላ ሰው ሞት ምክንያት የሚከፈል ካሳ፤
- ስጦታው የመቀጠር፣የኪራይ ወይም የንግድ ሥራ ገቢ ካልሆነ በስተቀር በስጦታ ወይም በውርስ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ ወይም ሀብት፤
- በትምህርት ተቋም ውስጥ ትምህርትን በነፃ ለመከታተል የሚፈፀም ክፍያ፤
- ለቀለብ ወይም ለህፃናት ድጋፍ የሚሰጡ ክፍያዎች፤
- ድርጅቱ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር የማይገናኝ የንግድ ሥራ ገቢን ሳይጨምር ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የሚያገኘው ገቢ፤
- ገንዘብ በሚቆጠርበት ጊዜ ለሚደርሰው ጉድለት ማካካሻ በሚሆን መጠን ብቻ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው እና ለዚሁ ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የጥሬ ገንዘብ ማካካሻ ክፍያ፤
- በኢትዮጵያ ፀንቶ በሚሰራበት ሕግ መሠረት በተለይ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረገ ገቢ፤
- ለመኖሪያ ቤት ሠራተኞች የሚከፈል ደመወዝ፤
- በነዳጅ ሥራ ላይ የተሰማራ ሥራ ተቋራጭ ለንዑስ ሥራ ተቋራጮች የሚፈፅመው ክፍያ።
- ለኢኮኖሚ፣ ለአስተዳደራዊ ወይም ለማህበራዊ ምክንያቶች አንድን ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ሊያደርግ እንደሚችል ባመለከተው መሠረት የሚከተሉት ገቢዎች ከገቢ ግብር ነፃ ናቸው፤
    - በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶች ለእውቀት ሽግግር ከውጭ ሀገር ለሚያስመጧቸው ባለሙያዎችከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚከፈላቸው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፤
    - በማንኛውም የአስራሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ለአንድ ቀጣሪ ሳያቋርጥም ሆነ በተደጋጋሚ ከሠላሳ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ያገለገለ ማንኛውም ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ የሚያገኘው ገቢ፤ሆኖም በአስራሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ አንድ ሰው በተደጋጋሚ ለአንድ ቀጣሪ የሰጠው አገልግሎት ሲደመር ከአንድ ወር የሚበልጥ ከሆነ ተቀጣሪው የሚከፍለው ግብር የሚታሰበው በመጨረሻው ቅጥር ባገኘው ገቢ ላይ ብቻ ይሆናል።
    - "ባለሙያ ያልሆነ ተቀጣሪ" ማለት መደበኛ የሙያ ሥልጠና ያልወሰደ ልዩ ሙያ በሚጠይቁ ማሽኖችና መሣሪያዎች የማይጠቀም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ከ30 ቀናት ለማይበልጥ ጊዜ የተቀጠረ ግለሰብ ነው።

- ከግብር ነጻ የተደረገው አሠሪው ሠራተኛው ሲታመም ለሠራተኛው ህክምና አገልግሎት የከፈለለት ገንዘብ በሠራተኞች የጤና መድን አቅድ መሠረት አሠሪው ለሠራተኞች ጥቅም የሚከፍለውን አረቦን ይጨምራል።
- ለኮንስትራሽን ማሽነሪ ኦፕሬተሮች የሚከፈለው ውሎ አበል ከ 25 ኪ.ሜ. ባነሰ ወይም በበለጠ ርቀት ቢሆንም የተከፈለው የውሎ አበል ከግብር ነፃ ይሆናል፤
- የመንግስት መስሪያ ቤት ለተሻሚዎች እና ለተቀጣሪዎች ከመደበኛ የስራ ቦታቸው ውጭ ከ 25 ኪ.ሜ. በላይ ርቀው በመሄድ ለሚያከናውኑት ሥራ የሚከፈል የቀን ውሎ አበል ሙሉ በሙሉ ከግብር ነፃ ነው

## 3.1.2 በገደብ ከገቢ ግብር ነፃ የተደረጉ ገቢዎች

<u>የትራንስፖርት አበል፡-</u>

- **በሥራ ውል መሠረት** ሥራውን ከቦታ ወደ ቦታ በመዘዋወር የሚያከናውን ተቀጣሪ ለአንድ ወር ጉዞ የሚከፈለው የትራንስፖርት ወይም የነዳጅ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከጠቅላላ የወር ደሞዙ ከ 1/4 ኛ ባልበለጠ ብቻ ሲሆን የደመወዙ 1/4 ኛ ከብር 2 ሺ 200 በላይ ከሆነ ታክስ ይከፈልበታል።
- አንድ ተቀጣሪ ከመኖርያ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲሁም ከሥራ ቦታው ወደ መኖሪያ ቤቱ ለመሄድ የነዳጅ ወጪ ወይም በጥሬ ገንዘብ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል 600 ብር ብቻ ነው፤
- አንድ ተቀጣሪ ሥራውን ለማከናወን ከመደበኛው የሥራ ቦታ ከሚገኝበት ውጪ ሲንቀሳቀስ ለትራንስፖርት ወጪ ከግብር ነፃ የሚሆነው በስራላይ ባለው የትራንስፖርት (የአየር፣የውሃ እና የየብስ) ዋጋ ሊበልጥ አይችልም።
- አንድ የውጭ አገር ዜጋ ስራውን ለማከናወን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣና የውል ዘመኑን ጨርሶ ከሀገር ሲወጣ የሚከፈለው የትራንስፖርት ወጪ ከገቢ ግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው በተፈጸመው የቅጥር ውል መሰረት እና የአየር፣ የውሃ እና የየብስ ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ ታሪፍ መሰረት ሆኖ ከግብር ነፃ የሚሆነው ለግል መገልገያ ዕቃዎች የሚከፈለው የጭነት ሂሳብ ከ 300 ኪሎ ግራም ሊበልጥ አይችልም

<u>የስራ ቦታ አስቸጋሪነት የሚከፈል አበል ፡</u>

- የሥራ ቦታ አስቸጋሪነት ከፍተኛ ሙቀት ወይም ለኑሮ አስቸጋሪ በመሆኑ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ምክንያት በተቀጣሪው ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈል አበል ሲሆን ፡-
  - በሥራው ቦታ አስቸጋሪነት ምክንያት የሚከፈል አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሠረት(አንደኛ ደረጃ ቆላ ከሆነ ከደመወዙ 40%፣ ሁለተኛ ደረጃ 30% እና ሶስተኛ ደረጃ 20%) የሚከፈል ነው።
  - በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ማይተዳደሩ መ/ቤቶች እና የግል ድርጅቶች ተቀጣሪ ወይም ሹመኛ ጨምሮ በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናል።

<u>የስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት የሚከፈል አበል፡-</u>

- ሥራው ሁኔታ ለጨረር፣ ለበሽታ፣ለኬሚካል፣ ወዘተ በጤና ደህንነት ላይ ጉዳት ማካካሻ የሚከፈል፤-

- **በሥራ ሁኔታው አስቸጋሪነት ምክንያት ለሠራተኛው የሚከፈል አበል፤** (ዝቅተኛው 25%፣ ለመካከለኛ 40%፣ ለከፍተኛ 60%)፤ ሲሆን የጉዳት ደረጃውን መለካት የማይቻል ከሆነ ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ ከ 25% (ሃያ በአምስት መቶ) ባልበለጠ መጠን ከገቢ ግብር ነፃ ይደረጋል።
- በስራ ሁኔታ አስቸጋሪነት ምክንያት ለሰራተኛ የሚከፈል አበል የስራው ሁኔታ ስለሚያደርሰው ችግር ከሚመለከተው አካል ማስረጃ መቅረብ ይኖርበታል።

<u>የውሎ አበል፡-</u>

- አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ሥራ ለማከናወን መበደኛ የሥራ ቦታ ከሚገኝበት ከተማ ውጪ ከ 25 ኪ.ሜ. በላይ ርቆ ሲሄድ ለመኝታ፣ምግብ እና መጠጥ እና ተዛማጅ ወጪ የሚከፈል ነው፤
- ለማንኛውም ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይም ምክትል ሥራ አስኪያጅ የሚከፈለው የውሎ አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው 1000 ብር ወይም የደሞዙ 5% ከሁለቱ ከፍተኛ ባልበለጠ ብቻ ሲሆን የአልጋ አበል በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራት እና ለመሳሰሉት የሚሰጠው የውሎ አበል ከግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 600 ወይም የደሞዙ 3% ከሁለቱ ከፍተኛ ባልበለጠ ብቻ ነው።
- አንድ ተቀጣሪ የሚከፈለው የቀን ውሎ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው ከብር 500 ወይም ከደሞዙ 4% ካልበለጠ ብቻ ነው።
- አንድ ተቀጣሪ የአልጋ አበል በደረሰኝ የሚወራረድለት ከሆነ ከግብር ነፃ ሲሆን፤ ለቁርስ፣ ለምሳ፣ ለእራትና ለመሳሰሉት 300 ብር ወይም ከደሞዙ 2.5% ሆኖ ከሁለቱ ከፍተኛ ባልበለጠ ብቻ ነው።
- የማንኛውም ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ወይም ም/ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ስራ ጋር በተገናኘ ወደ ውጭ ለሚያደርገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ለሌሎች ሰራተኞች /ተቀጣሪዎች በወሰነው ልክ ላይ 20 በመቶ ተጨምሮበት ነው፤
- አንድ ተቀጣሪ የተቀጠረበትን ስራ ለማከናወን ወደ ውጭ አገር ለሚደረገው ጉዞ የሚከፈለው የውሎ አበል ከገቢ ግበር ነፃ የሚሆነው መንግስት ከተሻሚዎች ውጪ ለሌሎች ተቀጣሪዎች በወሰነው የውሎ አበል ልክ ባልበለጠ ብቻ ይሆናል

<u>ምሳሌ አንድ</u>

ወ/ሮ አልማዝየ YXZ ጨርቃ ጨርቅ እንጂነሪንግ ኩባንያምክትል ስራ አስኪያጅ ሆነው የሚሰሩ ሲሆን በወር 50 ሺህ ብር ደመወዝ ይከፈላቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም የቤት አበል በወር 5 ሺህ ብር፣ የስልክ ጥሪ ወጪ 200፣የትራንስፖርት መጓጓዣና መዘዋወሪያ አበል 7500 ብር ፣ ከቤት ወደ ሥራና ከሥራ ወደ ቤት 1000 ብር እና ለመስክ ስራ ለ 10 ቀናት ለተንቀሳቀሱበት የውሎ አበል ተከፍሏቸዋል።

ጥያቄ አንድ፡- ታክስ የሚከፈልባቸው ገቢዎች የትኞቹ ናቸው?

ጥያቄ ሁለት፡- ታክስ የማይከፈልባቸው ገቢዎች የትኞቹ ናቸው?

ጥያቄ ሦስት፡- ታክሱ ስንት ነው?

ጥያቄ አራት፡- የተከፈላቸው ውሎ አበል ምን ያህል ነው?

ጥያቄ አምስት፡- ከታክስ በኋላ የተገኘ ገቢ ስንት ነው?

<u>መልስ 1፡- ታክስ የሚከፈልባቸው ገቢዎች</u>

የትራንስፖርት መጓጓዣና መዘዋወሪያ አበል 50,000 x1/4= 12,500 ሲሆን የደሞዙ ¼ ከ 2200 መብለጥ ስለሌለበት 7500 -2200 =5,300 ይሆናል ማለት ነው

ከቤት ወደ ሥራና ከሥራ ወደ ቤት 1000-600 = <u>400</u>

በጠቅላለው ታክስ የሚከፈልበት ገቢ=50,000 +5,000+5,300+400 =<u>60,700</u>

መልስ 2፡- ታክስ የማይከፈልባቸው ገቢዎች 200+2,200+600 =<u>3,000</u>

መልስ 3፡- የሚከፈለው ታክስ መጠን= 60,700 x 35/100 - 2,050 =<u>19,195</u>

መልስ 4፡- ለስራ አስኪያጅ ወይም ለምክትል ስራ አስኪያጅ የሚከፈለው የቀን ውሎ አበል ከገቢ ግብር ነፃ የሚደረገው 1000.00 ብር ወይም ከደመወዙ 5% ሆኖ ከሁለቱ ከፍተኛ ከሆነው ባልበለጠ ብቻ ይሆናል።

ስለዚህ 50,000 x 5% = <u>2,500</u> የቀን ውሎ አበል 1000 ሳይሆን 2,500 ነው ምክንያም ከሁለት አንዱ የበለጠውን ስለሚልየ 10 ቀናት የሥራ ቆይታ x 2,500 = 25,000 የውሎ አበል ያገኛል ማለት ነው።

ጠቅላላ ገቢ = 50,000+5,000+200+7,500+1,000+25,000= 88,700.00

መልስ 5፡- ከታክስ በኋላ ያለው ገቢ = 88,700-19,195 = **<u>69,505</u>**

ለተቀጣሪ በነፃ ለሚቀርብ ምግብና መጠጥ

- በማዕድን ማውጣትና ፍለጋ፣በማኑፋክቸሪንግ እና በግብርናና ሆርቲካልቸር ስራ ላይ ለተሰማሩ በአንድ ወር ለደመወዝ በሚያወጣው ከአጠቃላይ ደመወዝ ወጪ 30% ሳይበልጥ እና
- ሆቴሎች፣በሬስቶራንቶች ወይም በሌሎች የምግብ አገልግሎት ስራ ላይ ለተሰማሩ በአንድ ወር ለደመወዝ በሚያወጣው ከአጠቃላይ ደመወዝ ወጪ 20% ሳይበልጥ)
- ለተቀጣሪዎች የሚቀርብ የደንብ ልብስ እና የሥራ መገልገያ።
- በዓይነት ጥቅሞች ላይ የሚከፈለው ጠቅላላ ግብር በማንኛውም ሁኔታ ተቀጣሪው በወሩ ከሚያገኘው የደመወዝ ገቢ 10% (አስር በመቶ) አይበልጥም።

**በውጭ ሀገር ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ**

- **ግብርን ቀንሰው የማስቀረት ግዴታ ከሌለባቸው ቀጣሪድርጅቶች ወይም ኢንባሲዎች የሚሰራ ሰው ራሱ ግብሩን ቀንሶ ማስቀረት/መክፈል አለበት፤**
- **በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ተቀጣሪ በውጭ አገር በመቀጠር ገቢ ያገኘ እንደሆነና ግብር የከፈለበት ከሆነ ግብር ማካካሻ ያገኛል፤**

### 3.2 ከመቀጠር ገቢ ጋር የተያያዙ ሌሎ ችድንጋጌዎች

- ማንኛውም ቀጣሪ ለተቀጣሪው ከሚከፍለው ደመወዝ ላይ ሥራ ግብሩ ቀንሶማስቀረትና  መክፈል አለበት፤

- ተቀጣሪው ከአንድ በላይ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ካለው እና በአንደኛው  ቀጣሪ ይኼው  ከታወቀ  በጠቅላላው ገቢ ላይ ተመስርቶ ግብሩን  ቀንሶ በማስቀረት መክፈል አለበት፤
- ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር በቀጣሪው ተቀናሽ መደረግ ካለባቸው ሌሎች ግዴታዎች ቅድሚያ አለው፤
- ግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ በአንድ ሠንጠረዥ ውስጥ ከሚወድቁ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ገቢ ያገኝ እንደሆነ ሁሉም ገቢዎች ተጣምረው በዚያው ሠንጠረዥ ሥር የዓመቱን ግብር ይከፍላል፡፡

## <u>ሙከራ</u>፡- አራት

ሠልጣኞች ከመቀጠር ከሚገኙ ገቢ ላይ ከታክስ ነፃ የተደረጉ እና በገደብ ከታክስ ነፃ የተደረጉትን ይዘርዝሩ?

### ክፍል አራት

### 4.1 የወጪ መጋራት

ማንኛውም በመንግስታዊ ተቋም የከፍተኛ ትምህርቱን ያጠናቀቀ ምሩቅ ተማሪ ወጪን በመጋራት መርህ ላይ የተመሰረተ የትምህርት፣ስልጠናና አገልግሎት ክፍያ መፈጸም ይኖርበታል ፡፡

ክፍያው የሚፈጸመው ከምረቃ በኋላ ከሚገኝ የደሞወዝ ገቢ ወይም ሌላ ገቢ ላይ ተከፋይ በሚሆን ግብር ይሆናል ፡፡ (የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 351/1995 አን 56)

ከ 1996 ዓ.ም.የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ መንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ከነበሩበት ዓመት ጀምሮ ተፈጻሚ የሆነ ነው ፡፡

### 4.2 የወጪ ድርሻ

መንግስትለምግብናለመኝታየሚያወጣውንወጪ.ሙሉበሙሉ እና ለትምህርት ከሚወጣው ውጪ ለመነሻ 15% ያላነሰ ተሰልቶ ተጠቀሚዎች ይጋራሉ፡፡

ተጠቃሚው ሊጋራቸው የማይገቡ ወጪዎች ፣

- በትምህርት፣ በምርምር ወይም በሰባቲካል እረፍት ያሉ መምህራንን ለመተካት የሚቀጠሩ የትርፍ ጊዜ መምህራን ደመወዝ
- የህክምና ባለሙያዎች የፕሪ-ክሊኒካልና የክሊኒካል አበል
- ለመስተንግዶ፣ለፕላንት ፣ለማሽነሪ እና ለመሳሪያ ግዢ፣ እድሳትና ጥገና ፣ለሀገር ውስጥ ለስልጠና፣ ለተሽከርካሪ ለሌሎች እንደተሽከርካሪ ላሉ መጓጓዣዎች መግዣ፣ለሕንፃ ፣ለቁሳቁስ እና ለተገጣጣሚዎች መግዣ ሌሎች ክፍያዎች

እንዲሁም በቀጥታ በተቋሙ ገቢ በማስገኘት ዓላማ ላይ የተሰማሩ ክፍሎች ሰራተኞች ደመወዝ ተጠቃሚው እንዲጋራቸው አይጠበቅም፡፡

## 4.3 የወጪ መጋራት ውልና አፈፃፀም

- ማንኛውም በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርት እንዲከታተል የተመደበ ተጠቃሚ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ በየትኛው የክፍያ ዓይነት ወጪ እንደሚጋራ ከተቋሙ ጋር ውል ይፈጽማሉ ፡፡
- ውል የሚፈፀመው፣ በጤናና በትምህርት ሙያ ለሚሰለጥኑና ለሚሰማሩ ተጠቃሚዎች መንግስት በሚመድባቸው ማንኛውም ቦታ በአገልግሎት ግዴታቸውን እንዲወጡ
- የወጪ መጋራትንበአገልግሎት እንዲወጡ ለተፈቀደላቸው ባለሙያዎች ለሰለጠኑበት ጊዜ እኩል የአገልግሎት ጊዜ በመስጠት ይኖርባቸዋል ፡፡
- እያንዳንዱ እስከ ምርቃ ወይም እስካቋረጡበት ጊዜ ድረስ የሚፈለግበትን የወጪ መጋራት ሂሳብ እና ጠቅላላ ለትምህርቱ የወጣውን ወጪ ተቋማት ለኢትዮጲያ ገቢዎች ጉምሩክ ባለስልጣን በየትምህርት ዘመኑ ከምረቃ በኋላ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ በቋሚነት ማሳወቅ አለባቸው፡፡
- አስቀድሞ የከፈለ ተማሪ ትምህርቱን ካቋረጠ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ ያለው ወጪ ታስቦ ቀሪው ተመላሽ ይሆንለታል፡፡
- በማንኛውም የትምህርት ሙያ የሚሰለጥን ባለሙያ ትምህርቱን ሳያጠናቅቅ በማንኛውም ምክንያት ቢያቋርጥ እስካቋረጠበት ጊዜ ድረስ የተጠቀመውን ወጪ መክፈል ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ትምህርቱን ያቋረጠው በሀገራዊ ጥሪዎችና ተልዕኮዎች ከሆነ ክፍያው መሰረዝ ይኖርበታል፡፡
- በትምህርት ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ማንኛውም የመንግስት ትምህርት ቤት፣ ቴክኒክና ሙያ ማስልጠኛ ፣የመምህራን ማስልጠኛ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሌሎች የመንግስት ማስልጠኛ ኢንስቲትዩት ተመድቦ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባ ካላገኘም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ በማሳወቅ መረጃ በመያዝ እና በማቅረብ የወጪ መጋራቱን በገንዘብ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
- በጤና ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር/የክልል ጤና ቢሮ በሚመድበው ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኝ የመንግስት የጤና ተቋማት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ሲኖርበት ምደባ ካለገኘ ከጤና ጥበቃ ሚ/ር ፣ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከክልል ጤና ቢሮ ማስረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡ በሚያቀርበው መረጃ መነሻነት የውጪ መጋራት ክፍያ ግዴታውን በገንዘብ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
- በአገልግሎት ግዴታውን ለመወጣት ውል የፈፀመ ተጠቃሚ እንደተመረቀ ምደባ በወቅቱ አለማግኘቱን ከሚመለከተዉ አካል ማለትም ትምህርትን በሚመለከት እንደ አግባብነቱ ከክልል ትም/ቢሮ ወይም ከትምህርት ሚኒስቴር የተሰጠውን መረጃ ማቅረብ የማይችል የትምህርት ባለሙያ እና ጤናን በሚመለከት ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከክልል ጤና ቢሮ መረጃ ማቅረብ የማይችል የጤና ባለሙያ በመንግስት ተቋም በራሱ ተቀጥሮ ቢሰራ ግዴታውን በአገልግሎት እንደተወጣ አይቆጠርም፡፡ ግዴታውን በገንዘብ ከነመቀጫው እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምደባ አለማግኘቱን ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል የትምህርት ባለሙያ በመንግስት ትምህርት ቤቶችና ተቋማት በመምህርነት ሙያ እንዲሁም ጤናን በሚመለከት በመንግስት ጤና ተቋማት ተቀጥሮ የስራ የጤና ባለሙያ ግዴታውን በአገልግሎት እንደተወጣ ይቆጠራል፡፡

- የወጪ መጋራቱን ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት እንዲወጣ የሚፈለግ ማንኛውም ተጠቃሚ ግዴታውን በአገልግሎት መወጣት ይኖርበታል፡፡
- መንግስት በመደበው ቦታ አገልግሎት መስጠት ያልቻለ ተጠቃሚ በውሉ ላይ ተገለፀውን/የትምህርት 15%፣የምግብ እና የመኝታ ሙሉ በሙሉ ወጪ እና የዚህን ወጪ 50% ቅጣት ጨምሮ ይከፈላል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ አገልግሎት ሰጥቶ ያቋረጠ ተጠቃሚ ያገለገለበት ዘመን ታስቦ ቀሪውን ክፍያ ከነቅጣቱ እንዲከፍል ይደረጋል ፡፡ ተጠቃሚው ቀደም ሲል በሌላ መስክ ተሰማርቶ በገንዘብ መክፈል የጀመረ ከሆነ ቀሪውን ክፍያ ብቻ መንግስት በሚመድበው ቦታ በአገልግሎት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡
- በማንኛውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በመንግስት ትምህርት ቤቶች ፣በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ በመምህራን ማሰልጠኛ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሌሎች የመንግስት የማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት በመምህርነት ሙያ ወይም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በኃላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል እና ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ሰራዊት አባል የሆኑ ብቻ በምደባም ይሁን በቅጥር በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራቱ በአገልግሎት ሊያዝላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በከፊል አገልግሎት ሰጥተው ካቋረጡ ቀሪውን የወጪ መጋራት ግዴታቸውን ከነመቀጫው ገንዘብ በመክፍል እንዲወጡ ይደረጋል፡፡
- በሀገር መከላከያ ሰራዊት ፣በፌደራል፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ፣ በክልል እና ማረሚያ ቤቶች በፖሊስ ሰራዊት አባልነት ብቻ አገልግሎት የሰጡ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ከሰጡበት ተቋም በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከዕዳ ነጻ ስለመሆናቸው ከባለስልጣኑ ማስረጃ በማቅረብ የትምህርት ማስረጃቸውን ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ማግኘት ይችላል፡፡
- ማንኛውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በምደባም ይሁን በቅጥር በመምህርነት ወይም በጤና ዘርፍ ተመርቀው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በመስራት ላይ እያሉ መንግስት ለስራ ፈልጓቸው በሹመት የተመደቡ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ በማቅረብ ሹመት ከማግኘታቸው በፊት የሰሩበት ጊዜ በአገልግሎት ታስቦ ቀሪውን ግዴታ ያለቅጣት በገንዘብ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡

## 4.4 ተጠቃሚው ክፍያውን በገንዘብ ለመክፈል ያሉ አማራጮች፡-

- ትምህርቱን ጨርሶ ወይም አቋርጦ ከቆየ ከአንድ አመት የእፎይታ ጊዜ በኋላ በግብር መልክ ከደመወዙ ወይም ከገቢው ላይ ቢያንስ ከመቶ አስር /10%/ ተቀናሽ እየተደረገ ሊከፍል ይችላል፡፡
- ለተጠቃው ትምህርት በሚከታተልበት በእያንዳዱ አመት የሚፈልግበት ክፍያ በቅድሚ ወይም
- ተጠቃው እንደተመረቀ ወይም ትምህርቱን እንዳቋረጠ በእፎይታ ጊዜው ውስጥ ክፍያውን በሙሉ በአንድ ጊዜ ሊከፍል ይችላል ፡፡

## 4.5 የእፎይታ ጊዜ

ተጠቃሚው ከተመረቀበት ወይም ትምህርቱን ካቋረጠበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ሥራ ቢይዝም ባይዝም ክፍያ ለመጀመር የአንድ ዓመት የእፎይታ ጊዜ ይኖረዋል ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ሥራ ካልሠራና ገቢ ካላገኘ ከሁለተኛው ዓመት መጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለስድስት ወራት ብቻ የእፎይታ ጊዜ ይሰጣል ፡፡

## 4.6 ማበረታቻ

- ጠቅላላ የውጪ መጋራት በቅድሚያ ለሚከፍል ተጠቃሚ 10%
- በየሰሚስተሩ ወይም በየዓመቱ ቅድሚያ ለሚከፍል 5%
- ከምረቃ በኋላ በእፎይታ ጊዜ እስከ አንድ ዓመት ለሚከፍል 3% ተቀናሽ ይደረግለታል ፡፡

## 4.7 የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ እና ስለቀጣይ ስልጠና ሥርዓት

- የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራትበአገልግሎት እንዲከፈሉ የሚጠበቅባቸው ተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት ግዴታ እስኪወጡ ወይም በገንዘብ ግዴታ የገቡ ተጠቃሚዎች ክፍያ እስኪያጠናቅቁ ወይም ለክፍያው የባንክ ዋስትና እስኪያቀርቡ ጊዜያዊም ሆነ ዋናውን የትምህርት ማስረጃና ትራንስክርፕት /ኦፊሻልን ጨምሮ/ የትምህርት መረጃ አይሰጥም ፡፡
- ማንኛውም የመንግስት ሆነ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም በሙያው አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ያለበትን ተመራቂ አገልግሎት መስጠቱን እንዲሁም ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የገባ ክፍያውን ሳያጠናቅቅ ለቀጣይ ከፍተኛ ትምህርት መቀበል የለበትም ፡፡

## 4.8 የወለድ አከፋፈልና መጣኔ

ተጠቃሚው የሚከፍለው የወጪ መጋራት ክፍያ ወለድ የሚታሰብበት ሲሆን ወለዱ መታሰብ የሚጀምረው ከእፎይታ ጊዜ በኋላ ነው፡፡ የወለዱ መጠንም ተጠቃሚው ከተቋሙ ጋር በፈረመባቸው የትምህርት ዘመናት የተቀማጭ ገንዘብ አማካይ የወለድ መጣኔ ይሆናል፡፡

<u>ለምሳሌ፡-</u>

ተጠቃሚው የፈጀበት የትምህርት ጊዜ አራት አመት ሆኖ የተቀማጭ ገንዘብ የወለድ መጣኔ የሁለት አመት 3%ቢሆን የቀረው ሁለት አመት ደግሞ 4%ቢሆን ክፍያው የሚታሰብበት የወለድ መጣኔ፡-

$$\frac{2(3) + 2(4)}{4} = \frac{14}{4} = 3.25$$ ይሆናል፡፡

ተጠቃው የፈጀበት የትምህርት ጊዜ አምስት አመት ሆኖ የተቀማጭ ገንዘብ የወለድ ምጣኔ የሁለቱ አመት 4 ቢሆን የሦስቱ አመት ደግሞ 5 ቢሆን ክፍያው የሚታሰብበት የወለድ ምጣኔ ፡-

$$\frac{2(4) + 3(5)}{5} = \frac{23}{5} = 4.6$$ ይሆናል፡፡

- የወለዱ ስሌት እና አከፋፈል የማንኛውም የባንክ ብድር ወለድ በሚታሰብበትና በሚከፈልበት ዓይነት ዋናው እዳና ወለዱ ተለይቶ መሰላት፣ መክፈልና መሰብሰብ አለበት ፡፡

ዕዳን ለመክፈል ዋስ ስለማቅረብ

ተጠቃሚው የወጪ መጋራት ክፍያ ዕዳውን ክፍሎ ሳይጨርስ ከኢትዮጵያ ውጭ የሚሄድ ከሆነ ወይም ዋናውን/ኦርጅናል/የትምህርት ማስረጃውን ከጠየቀ፡-

- ዕዳውን በአንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ማጠናቀቅ ይኖርበታል

- ዕዳውን በአንድ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ክፍሎ ማጠናቀቅ ካልቻለ በእግሩ ተተክቶ እዳውን ከነወለዱ በየወሩ የሚከፍልለት የባንክ ዋስትና ማቅረብ ይኖርበታል

- ዕዳውን ከነወለዱ የሚከፍልለት የባንክ ዋስትና በማቅረብ ከ 15 ዓመት ባልበለጠ ዕዳውን ከፍሎ ማጠናቀቅ አለበት።

**የወጪ መጋራት ስሌት**

ለማስላት መሠረት የሚደረግባቸው ነገሮች

I. የተመረቀበት ዘመን፣
II. በምረቃ ወቅት የነበረው የባንክ ቁጠባ መጣኔ፣
III. የእፎይታ ጊዜ።

ምሳሌ:- 2005 ዓ.ምሰኔ 30 የተመረቀ ተማሪ አጠቃላይ 20 ሺህ ብር የወጪ መጋራት ብር ቢኖርበት ታኅሣሥ 30/2013 ዓ.ምላይ ሙሉ ክፍያ ለመክፈል ቢፈልግ አጠቃላይ ክፍያው ስንት ይሆናል?

I. የተመረቀበት ዘመን =ሰኔ 30/2005 ዓ.ም
II. በምረቃ ወቅት የነበረው የባንክ ቁጠባ ምጣኔ = 4% ቢሆን (ግምታዊ)
III. የእፎይታ ጊዜ 1 ዓመት (2006) ይሆንና ከ 2007 ጀምሮ ታክሱ የሚሰላ ይሆናል።

$$\text{ወለድ} = \frac{\text{ታክስ X ወር X የባንክ ቁጠባ መጣኔ}}{12}$$

$$\frac{20,000*78*0.04}{12}$$

ወለድ= 5,200.00

ጠቅላላ ክፍያ= ታክስ  ወለድ

ጠቅላላ ክፍያ = 20,000 +5,200

ጠቅላላ ክፍያ= 25, 200.00

## 4.9 የአሠሪዎች ግዴታ

ማንኛው አሰሪ፡-

- የቀጠራቸውን ተጠቃሚዎች ዝርዝር ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመወከለው የማስታወቅ
- በገንዘብ ለመክፈል ግዴታ ከገቡ ተጠቃሚዎች የሚፈለግባቸውን እዳ የሚያሳይ ማስረጃ ከተጠቃሚዎቹ በመቀበልና ስለ ትክክለኛነቱ ከባለሥልጣኑ በማረጋገጥ በየወሩ ከጥቅል ደመወዛቸው ቢያንስ 10% እየቀነሰ ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት ሰላሳ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚወክለው የመክፈል
- ተጠቃዎች ከተቋሙ የተሰጣቸውንና የሚፈለግባቸውን እዳ የሚያሳየውን ማስረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ካልሆኑ የጥቅል ደመወዛቸው አንድ ሶስተኛ እየቀነሰ ለባለስልጣኑ ወይም ለሚወክለው ገቢ የማድረግ ፣
- ገንዘብ በመክፈልም ሆነ አገልግሎት በመስጠት እዳቸውን ከፍለው ያጠናቀቁ ተጠቃሚዎችን ዝርዝር ክፍያው በተጠናቀቀበት ወር ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚወክለው የማሳወቅ

- አገልግሎት በመስጠት እንደሚከፍሉ ተገልጾ የተመደቡለትን ተጠቃሚዎች ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማሰራትና አገልግሎት ካቋረጡ ሙሉ ለሙሉ ማቋረጣቸውን በማረጋገጥ ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ለትምህርት ሚኒስቴር ለመደባቸው ሚኒስቴር መስርያ ቤት የማሳወቅ ግዴታ አለበት ።

የክትትልና ቁጥጥር ተግባር

ባለስልጣኑ ወይም የወከለው ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት

- ተጠቃሚዎችን ቀጥሮ  የሚያሰራ የመንግት ሆነ  የግል አሰሪ በደንቡ የተሰጠውን  ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ ስለመሆኑ  የቅጥር እና የክፍያ ሰነዶችን በመመርመር በማጣራትና በመከታተል
- እንደ አስፈላጊነቱም የወጪ መጋራት ክፍያው አሰባሰብ በተገቢው ሁኔታ እንዲፈፀም ለአሠሪው አስፈላጊውን የምክርና ቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት
- አሠሪው ወይም በግሉ የሚሠራ ተጠቃሚ ከገቢ ላይ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያውን ሳይፈጽሙ ከቀሩ የገቢ የግብር የመክፍል ግዴታውን ላልተወጣ ግብር ከፋይ በሚሰጠው ዓይነት የክፍያ ውሳኔ ማስታወቂያ አዘጋጅቶ ለአሰሪው ወይም ለተጠቃሚው እንዲደርስ ማድረግ
- አሰሪውም ሆነ ተጠቃሚው የተጣለባቸውን ኃላፊነት ካልጠወጡ ከገቢ ላይ ተቀንሶ ለባለስልጣኑ ገቢ ባልተደረገው ገንዘብ መጠን ፤ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጫ ጭምር ተጠያቂ እንደሚሆኑ በመግለጽ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ አለበት

ተመላሽ ጥያቄ አቀራረብና አፈጻጸም

- የወጪ መጋራት ክፍያ አስቀድሞ የከፈለ ተጠቃሚ ትምህርቱን በማቋረጡ ምክናያት ያልተጠቀመበት ገንዘብ እንዲሁም መከፈል ከሚገባው በላይ የወጪ መጋራት ክፍያ የፈጸመ ተጠቃሚ በስህተት በብልጫ የከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግለት አስፈላጊ ከሆኑ ማስረጃዎች ጋር ክፍያው ለተፈጸመበት የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ( ውክልና ለተሰጠው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት የከፈለ የስርዓቱ ተጠቃሚ በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ) ጥያቄውን ማቅረብ ይችላል ።

## ሙከራአምስት

ሰልጣኞች የወጪ መጋራት አከፋፈል ሥርዓት ያስረዱ?

## ሙከራ ስድስት

ሠልጣኞች ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ እና የወጪ መጋራት ምንነት በመረዳት መብትና ግዴታዎን ይዘርዝሩ

### ማጠቃለያ

ግብር የአንድ ሀገር መንግስት ዋነኛና አስተማማኝ የገቢ ምንጭ በመሆኑ ከመቀጠር ከሚገኝ ገቢ (ሠንጠረዥ "

ሀ")ከቅጥርውልጋርበተያያዘየሚያገኘውደመወዝ/ምንዳ፣አበል፣ጉርሻ፣ኮሚሽን፣የመልካምሥራአፈፃፀምማበረታቻስጦታወይም ሌላየአገልግሎትዋጋክፍያ፣ ተቀጣሪው ከስራ ሲቀነስ ወይም ከስራ ሲለቅ ወይም ስራን እንዲለቅ ለማግባባት የሚከፈል ገንዘብ ወይም የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በፈቃደኝነት፣ በስምምነት፣ በዳኝነት ውሳኔ መሠረት በጥሬ ገንዘብ (በዓይነት) የተቀበለው ማንኛውም የገንዘብ መጠን ከታክስ ነጻ ከተደረገው ውጭ፣ እንደ ገቢ ተቆጥሮ ታክስ የሚሰላበት በመሆኑና የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራትም መንግስት ለትምህርትና ለሌሎች አገልግሎቶች ያወጣውን ወጪ መጋራት በመሆኑ ታክሱን የመሰብሰብ ኃላፊነት የተጣለባቸው አካላት ታክሱን በተቀመጠው ህግ መሰረት ለግብር ሰብሳቢው መ/ቤት በወቅቱገቢ እንዲያደርጉ እና ወጥነት ያለው አሰራር ሥርዓት እንዲኖር ለማስቻል ነው ።

**ማጣቀሻዎች**

*በዚህ ስልጠና ርዕስ የተጠቀምናቸው ማጠቀሻ አዋጆች ፤ደምቦች እና መመሪያዎች*

1. **የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር** 979/2008
2. **የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር** 1395/2017
3. **የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር** 983/2008
4. **ከገቢ ግብርነፃ የተደረጉ ገቢዎችአፈፃፀምመመሪያቁጥር** 1/2011
5. **የወጪ መጋራት ደንብ** 154/2000
6. **የወጪ መጋራት መመሪያ ቁጥር** 2/2009
7. የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ 351/1995